# በአዲሱ አመት የሚያስፈልገን የተቃውሞ ፖለቲካ ህዳሴ ነው!!(ክፍል 1)

**ዮናስ 09/22/13**

ዝርጠጣና መመፃደቅ የዚህች ሀገር ፖለቲካ መገለጫ እና ጣጣ ሆኖ እስከመቼ ይሆን የሚዘልቀው? ማብቂያና ማቆሚያው እኮ ይኸው እንደናፈቀን በርከት ያሉ አመታቶች ተቆጠሩ አይደል። በዚህ አዲስ አመት የምመኘውና በርካቶችም የሚጋሩት ምኞት የተቃውሞውን ፖለቲካ ህዳሴ ነው።

ሀገሪቷን እየመራ የሚገኘው ኢህአዴግ ላለፉት 22 ዓመታት መቼም አንዳች በጎ ነገር ሳይሰራና እንዲያውም የሚበዛው ስራ ህዝቡን ጠቅሞ እስካልተገኘ ድረስ ከቶውንም ቢሆን 22 ዓመታት ለመቆየት የሚያስችለው አንዳች ሃይል (ጠመንጃም ቢሆን) አለ ብሎ ማሰብ ከየዋህነትም በላይ አላዋቂነት ይመስለኛል።

የዚህም ጽሁፍ መነሻ ይኸው ከየዋህነትም በላይ የሆነው የአላዊቂነት ኢህአዴግን የተመለከቱ ትርክቶች ናቸው። ኢህአዴግን ያለአንዳች በጎ ነገርና ውጤት ለ22 ዓመታት ያቆመው ሃይል አለ ብለን ብንወስድ እንኳ ላለፉት 22 ዓመታት በተለይም ደግሞ ከምርጫ 97 በኋላ ስርዓቱን የሚያራክሱት የታቃውሞው ፖለቲካ መስመርተኞችና ቅጥረኞች እራሳቸውን ለማየትና ለመፈተሽ አንዳች ሙከራ አለማድረጋቸውና እራሳቸውንም ለመተቸት ሳይደፍሩ መሆኑ ደግሞ ስለ ህዳሴያቸው ያለንን ምኞት የበለጠ ያጠናክረዋል።

ሀገሬ ለሃይማኖታዊና ለማህበራሰባዊ አስተምህሮዎች እጅጉን የመቅረቧን ያህል ይህንኑ አስተምህሮዎዋን ተቃዋሚዎቹ ይናገሩታል እንጂ አይተገብሩትም። አራጋቢ ፕሬሶቹም እነሱ በፈሰሱበት ቢፈሱ እንጂ ገገርውን የሚተቹትን (በተጨባጭ መረጃም ሆነ በምናብ) እነርሱን ለመተቸትና ለመምከር ሲደፍሩ ማየትም ናፍቆናል። ዞሮ ዞሮ ፖለቲካውና ሙግቱ ለህዝቡና ለሃገር ከሆነ ይህ ደግሞ ከፕሬሱም ሆነ ከተቃውሞው ጎራ የሚጠበቅ ነበር። ግን አልሆነም። ስላልሆነም ይህ በቀናነትና በምክንያታዊነት ለሚመራ የተቃውሞ ፖለቲካ እና ፕሬስ የአዲሱ አመት ምኞታችን ቢሆን ተገቢነት አለው።

ከላይ እንደተመለከተው ዝርጠጣና መመፃደቅ መገለጫው የሆነው የተቃውሞ ፖለቲካና ትርክት አመታት ቢያስቆጥርም ያለፉት ዓመታትን ሁሉ ዝርጠጣና መመፃደቅ በዚህ ጽሁፍ አንስተን አንዘልቀውም። ሆኖም ግን ለዚህ ሃሳብ ጥሩ ማሳያ የሚሆነኝና መነሻ ምክንያት የሆኑኝን ትርክት ለዚሁ አዲስ አመት ከተበረከተች የአዲስ ጉዳይ መጽሄት ላይ አግኝቻለሁና ከጉዳዩ ጋር

ተያያዥነቱ የሰመረ ከመሆኑም በላይ የቅርብ ቀን ህትመት መሆኑና አንባቢያንም በቅርብ ሊያገኙት ከመቻላቸው አንፃር የማሳያ ምርጫዬ ተገቢ ነው ብዬ አስባለሁ።

ለወትሮው በቅንነት፣ በሚዛናዊነትና በምክንያታዊነት ስትተች፣ ስትመከር ፣ ስትነቅስ፣ ስታበረታታ የምናውቃት "አዲስ ጉዳይ" የተባለች መጽሄት እኛ በምንገምተው የኪራይ ሰብሳቢነት ምክንያት እነሱ ደግሞ በሚያውቁት ምክንያት በተለይ ካለፉት አምስትና ስድስት ሳምንታት ጀምሮ የዝርጠጣውና የመፃደቁን ፖለቲካ መስመር በማራገብና ገዢ ስርዓቱንም በተመሳሳይ በማራከስ ተግባር መጠመዱ የሚያሳዝነኝና ለእርሷም ተሃድሶ የአዲሱ አመት ምኞቴ ነው።

እንደሚታወቀው ርዕሰ አንቀፅ የሚባለው ነገር የጋዜጣው ወይም የመፅሄቱ አቋም ነው። ስለሆነም የመጽሄቷ አቋም የበለጠ ተብራርቶ የሚቀርብበት የአዲስ ጉዳይ አቢይ ጉዳይ አምድ "የፖለቲካ ለውጥ ያስፈልገናል" በሚል ርዕስ ስር የተነሳው ጉዳይ የመጀመሪያው መነሻዬ እና በዚህ ክፍል የምመለከተው አጀንዳ ነው።

ሁለተኛውና በሁለተኛው ክፍል ትርክት የምመለከተው ደግሞ በዚህችው የአዲስ አመት በረከት ሆና በቀረበችውና ብዙዎቹን አጀንዳዎች ከፖለቲካ እና አዲስ አመት ጋር አቀናጅታ ለንባብ ከበቃችው አዲስ ጉዳይ "ኢትዮጵያ በአዲስ አመት ምኞትና ተስፋ" በሚል ርዕስ ስር ዝርጠጣቸውና መመፃደቃቸው የተመለከተው የተቃውሞው ፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮችና የተደናቆረ ሃሳባቸውን ነው።

ይህን የተደናቆረ ሃሳብ የተደናቆረ ስለመሆኑ በአስረጂዎች አስደግፌ ሳቀርብ እንደው እነርሱን ለመተቸት ሳይሆን የአዲሱን አመት ምኞትና በእርግጥም በአዲሱ አመት የሚያስፈልገን የተቃውሞው ፖለቲካ መስመርተኞች ህዳሴ መሆኑን ለማመላከት ነው።

በዚህ አግባብ ወደመጀመሪያው አጀንዳዬ የማመራው "የፖለቲካ ለውጥ ያስፈልገናል!" በሚል በቀረበው አጀንዳ ላይ የተቃውሞውን ፖለቲካ መስመርተኞችና አራጋቢ ፕሬሶች የዝርጠጣና የመመፃደቅ ስነ ልቦና ሊያሳዩ የሚችሉ ነጥቦችን በማንሳት ነው።

የገዢ ስርዓቱ ግንባር ተጣማጆችና ፈጣሪዎች አራት ብሄራዊ ድርጅቶች መሆናቸው ቢያንስ እውነት ነው። "በእገሌና በእገሌ ፓርቲዎች መካከል መሸዋወድ አለ፣ እገሌ እገሌ የተባለውን የግንባሩን አካል በበላይነት እየተቆጣጠረው ነው …" የሚልና መሰል አሉባልታዎችን ትተን፣ ከአሉባልታም አልፈው እውነት ሆነው ቢገኙ እንኳን እንደጋዜጠኛ የአራት ፓርቲዎች ጥምረት የሆነውን ግንባር መካድና ኢህአዴግን የአንድ ፓርቲ አካል አስመስሎ ማቅረብ ለሁለት ስህተቶች ያጋልጣል።

የመጀመሪየው ከጋዜጠኝነት አግባብ መውጣትንና ይልቁንም “በጋዜጠኝነት ቆብ የሚንቀሳቀሱ የተቃውሞ ፖለቲካ ስብስቦች” የሚለው የገዢ ፓርቲውን ክስ እውነትነት ማረጋገጡ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ግንባር ብሎ ቀጣይ ሁለትና ከዚያ በላይ የሚለውን ሰዋሰዋዊ አግባብ ግንባር ብሎ አንድ ፓርቲ በመጥቀስ መጣረስ መሆኑም ስለዜሮ ድምር ፖለቲካ የደረሰን ሙያዊ ንቅዘት የሚያረጋግጥ ነው።

ይህን መንደርደሪያ ያነሳሁት አዲስ ጉዳይ “የፖለቲካ ለውጥ ያስፈልገናል!” ሲል ባሰፈረው ትርክት ኢህአዴግን የህወሃት ብቸኛ ሃብት አድርጎ በመፃፉና ለውጥ የሚያስፈልገው እራሱ የሚመፃደቀው ፕሬስና የተቀዳሚው ፖለቲካ መሆኑን ስለሚያመላክት ነው።

“ህወሃት /ኢህአዴግ በጠብመንጃ አፈሙዝ ረዳትነት ስልጣን ከያዘ በኋላ አገዛዙን በምርጫ አማካኝነት ህጋዊ ለማድረግ የሄደበት መንገድ ስልጣኑን ካጠናከረ በኋላ ለለውጥ ክፍት ላለመሆኑ አንዱ ምክንያት ሆኖ ይጠቀሳል።..?"

“ለህወሃት /ኢህአዴግ” የሰፈረው_ማብራሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ሙሉውን እና ከዚሁ” ህወሃት/ ኢህአዴግ” ጋር ተያይዘው የተከተሉት ነጥቦችን ከገዢው ስርዓት የፖለቲካ ለውጥ ይልቁንስ የሚያስፈልገን የተቃውሞው ፖለቲካ ህጻሴ ከመሆኑ አንፃር ወደኋላ እንመዝነዋለን።

በዚሁ ትርክት “ስልጣን ሙጥኝ ባይነት” በሚለው ንዑስ ርእስ ስር የሰፈሩት እና በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ ሊለውጥ ከሚገባው ባህል አንዱ የገዢ አካላት ስልጣንን የሙጥኝ ባይነት ነው።…. ኢህአዴግ .. በምርጫ ቢያሸንፍም ባይሸነፍም ስልጣኑን አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ስልጣኑን ለማጠናከር ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄዶች መከተሉ ነው።

…. የኢህአዴግ ተቃውሞን በአግባቡ ያለማስተናገድና ሃይልና ተንኮል በተቀላቀለበት ታክቲክ የመጨፍለቅ ባህሪው የሚመነጨውም ከዚሁ ስልጣኑን ላለመልቀቅ ካለው ስነ ልቦና ይመስላል። በሚል የተመለከቱት ነጥቦች ህጻሴ የሚያሻው የተቃውሞውን ፖለቲካ እና መስመርተኞች ዝርጠጣና መመፃደቅ የሚያሳዩና በዚህ ክፍል በዋናነት የምነመዝናቸው ናቸው።

ሌላውና በመግቢያዬ አካባቢ የጠቀስኩት ለሃይማኖታዊና ማህበረሰባዊ አስተምህሮችና ምሳሌዎች ይናገሩታል እንጅ አይተገብሩትም ከሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንፃር በዚህ ክፍል የምንቃኘው ሃሳብ “ኢህአዴግ ውስጡን ይፈትሽ፣ ይለወጥም” በሚለው ንዑስ ርእስ ስር “የህወሃት የማርክሲዝም ሌኒኒዝም (ማሌ) አስተሳሰብ መለወጥ አለበት የሚባለው አንደም ፓርቲው በውስጡ ዴሞክራሲያዊ

አስተሳሰብና እሴቶችን እንዲያሰርጽና ----- ፓርቲው ከዴሞክራሲ እሴቶች ይልቅ አምባገነናዊ አመለካከቶችንና አሰራሮችን የሙጥኝ ብሎ በመያዙ -------" በሚል የሰፈረውን ትርክት ነው።

ሌላም ስለታቃውሞው ፖለቲካ እና መስመርተኞች የአዲሱ አመት የህዳሴ ምኞታችን ማሳያ የሚሆነን ትርክት አለ። ይህ የቀረበው ደግሞ " የፓርቲውና የመንግስት ባለስልጣናትን የመለወጥ አስፈላጊነት" በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ነው።

"የፓርቲውን የትጥቅ ትግል ዘመን አመለካከት ትተው በዘመናዊ ዴሞክራሲያዊና የቴክኖሎጂ እሴቶች የታነፁ እንዲሆኑ መስራት የግድ ይላል። -------- ኢህአዴግ ያረጀ ያፈጀውን የርዕዮተ ዓለም ቅራቅንቦ ማራገፍ እስካልቻለ ድረስ ------" ይላል ለፓርቲውና ለመንግስት አመራሮች መለወጥ አስፈላጊነትን የተመለከተው ነጥብ።

መሬትን የተመለከተው ፖሊሲና የፀረ-ሽብርተኝነቱ አዋጅ በ "እና" ሳይሆን "ወይም" ተብሎ ከፕሬስ ህጉ ጋር በተለዋጭነት የቀረበውና "የተጠሉና የማያዛልቁ ህጎችንና ፖሊሲዎችን መለወጥ" በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር የሰፈረው ነጥብም ሌላው የተቃውሞውን ፖለቲካ መስመርተኞች ህዳሴ ያስመኘኝ ነጥብ ነው።

"የህዝብ ለውጥ" በተተረከበት አጀንዳ ላይ ከተዘረዘሩት በርከት ያሉ ጉዳዮች ውስጥ ደግሞ በትርክቱ ማሳረጊያ የሰፈረው "በሀገራችን አብዮቱ የወለደው የደርግ የግፍ አገዛዝና በአሁኑ ጊዜ በአረቡ አለም የሚካሄዱት ህዝባዊ አመጾችና ውጤቶቻቸው---።" ሳይጸነስ የጨነገፈውን አብዮት ዳግም የአዲስ አመት መሻት የተመለከተው ነጥብ በርግጥም በአዲሱ አመት የሚያስፈልገን የተቃውሞን ፖለቲካ እና መስመርተኞች ህዳሴ መሆኑን ያመላከተኝ ሲሆን ብዙ የተባለለትና በተለይም የአዲስ ጉዳይ የተለየ አጀንዳ መሆን የጀመረው በሃይማኖት ሽፋን የሚከናወነው የአክራሪነት ዝንባሌ በዚህም አጀንዳ ላይ እንደቀድሞው ሁሉ "መለወጥ ያለበትና የገገረውን ፓርቲ ጣልቃ ገብቷል" ኡኡታን የተመለከተውም ነጥብ የተቃውሞውን ፖለቲካ እና መስመርተኞች ህዳሴ ለመሻቴ በማሳያነት የምመለከታቸውና የትርክቱ መስፈሪያ የሚሆኑኝ ሚዛኖቼ ናቸው።

የመጀመሪያው ምዘናችን ስልጣንን በተመለከተ የቀረበውና "የገገር አካላትን ስልጣን የሙጥኝ ማለት በሚል የቀረበው ሀቲት ነው። በመሰረቱ እዚህ ላይ መታሰብ ያለበት የሀገሪቱ የስልጣን ምንጭ ምንድነው? የሚለው ጉዳይ ነው። ይህንን የተገነዘበው ተራኪም ወይም ደግሞ የሃገሪቱ የስልጣን ምንጭ ምርጫና ምርጫ ብቻ እንደሆነ የተገነዘበውና በዚሁም ባለፉት 5 ተከታታይ ሀገር አቀፍ ምርጫዎች ኢህአዴግ በድል ማጠናቀቁን የተገነዘበው ተራኪ ለሴራውና ዝም ብሎ እና ከመሬት ተነስቶ ለናፈቀው ለውጥ ገገር ስርዓቱን ከመኮርኮም ይልቅ በጠራ መስመር የሚጓዝና ገገር

ፕሮግራምና ስትራቴጂ ኖሮት በምርጫ መወዳደር የሚሻና የአቋራጭ ስልጣን ናፋቂ ያልሆነ የፖለቲካ ስብስብ ይኖር ዘንድ ቢማፀን የተሻለ በሆነ።

እንዲያው በደፈናው "ስልጣን የህዝብ እንጂ የፓርቲ አይደለም" በማለት የፖለቲካ ስህተት ውስጥ ባይገባ ጥሩ ነበር። ስልጣን የህዝብ ነው ሲባል የራሱ አሰራርና አካሄድ ያለው ፖለቲካ መሆኑም ሊታወቅ ይገባል። የኢህአዴግም ስልጣን የህዝብ መሆኑ በምርጫ በወከልነውና በፓርላሜንታዊ ስርዓታችን የሚገለፅ እንጂ ስልጣን በእያንዳንዱ ግለሰብ እጅ ይጨበጣል ማለትም እንዳልሆነ ልብ ሊባል እና ጉዳዩ ከተቃውሞው ፖለቲካ እና መስመርተኛው አለመታደስ ጋር የተያያዘ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

የርዕዮተ አለም ለውጥ የሚለውም ጉዳይ ተመሳሳይ ነው። "ኢህአዴግ ከዴሞክራሳያዊ እሴቶች ይልቅ አምባገነናዊ አመለካከቶችንና አሰራሮችን የሙጥኝ ብሏል።" ይለናል ተራኪው የሆነ ሆኖ ግን ከማርኪስስታዊ ሌኒናዊ አስተሳሰብ መላቀቅ የተሳነውና ለመታደስ ዝግጁ ያልሆነው የተቃውሞው ፖለቲካ እና መስመርተኞች ስለመሆናቸው ከራሳቸው ከተቃውሞው ፖለቲካ መንደር የወጡትን እና ይልቁንም በአመራር ደረጃ የሚገኙ አካላትን ማብራሪያ ማስታወሱ በቂ ነው። የፕ/ር በየነ ጴጥሮስንና የአቶ ግርማ ሰይፉን እንኪያ ሰላንቲያ፣ የአንድነቶቹን ኢንጅነር ዘለቀ ረዲና አቶ አስራት ጣሴን እሰጥ አገባ፣ የሰማያዊ ፓርቲን መመጻደቅና የአንድነት ፓርቲን ዝርጠጣ፣ የአንድነት ጊዜያዊ ኮሚቴና የመድረኩን ስብስቦች በተለይም የአቶ ቡልቻ ደመቅሳንና የአንድነቱን ሃብታሙ አያሌው፣ የአንድነትን ከመድረኩ ጋር የመቀጠል እና ያለመቀጠል ውሳኔ በተመለከተ የነበረ መዘረጣጠጥ "ከናንተ እኔ እሻላለሁ"፣ "ለፖለቲካና ለዴሞክራሲ ማን እንደኛ"፣ "ብሄርተኛና ትምክህተኛ"፣ "ተለጣፊና አና እርጅና የተጫነው ፖለቲካ"፣" ከእኛ ውጭ እኮ የፖለቲካ ፓርቲ የለም"፣ "የሰለማዊ ሰልፉ ፈር ቀዳጅ---"ለሚሉና ለመሳሰሉት ዝርጠጣና መመጻደቅ ሰለባ የነበሩትና ከሃገርና ከህዝብ ይልቅ ለግል ጥቅማቸው አድረው የነበሩት የተቃውሞው ፖለቲካ መስመርተኞች እነጂ ሌላ አልነበረም። ስለሆነም በአዲሱ አመት የሚያስፈልገን የጠራ ፕሮግራምና ፖሊሲ ይዞ ገዢውን ፓርቲ መገዳደር የሚችል ፓርቲ በመሆኑ ወይ አዲስ እንሻለን አልያም የነባሩን ተሃድሶ እንመኛለን።

ኢህአዴግን እና ባለስልጣናቱን እንዲሁም መንግስትን እና ባለስልጣናቱን በተመለከተም ተመሳሳይ ለወጥ ያስፈልጋል በሚል በተለይም የኢህአዴግን ርዕዮተ አለም መራገፍ የሚገባውና ያረጀ ያፈጀ ቅራቅንቦ እንደሆነ ተራኪው ቢገልፁም የገዛ በተቃውሞው ፖለቲካ ሽፋን በሽብር ወንጀል የተከሰሰውና ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው አንዷለም አራጌ የመስመሩን ተሃድሶ በተመለከተ ያነሳውን ነጥብ ማስታወሱ ለውጡ የቱ ጋር መሆን እንዳለበት በቀላሉ ለመረዳት ያስችለናል።

ቁጥር 9 ፋክት መጽሄትን ያነበቡ። "የሃምሌ ጨረቃ" በሚል ርዕሰ ስር የተቃውሞውን መንደር 16 ገመናዎቸ ያገኟቸዋል። ከነዚህ ገመናዎች ውስጥ እነሆ ተቃዋሚው ሃይል ባረጀውና ባፈጀው ማርክሳዊ ሌኒናዊ አስተሳሰብ መላቀቅ ያቃተው መሆኑን፤ ለህዝብና ለሃገር ሲል ሳይሆን ለግል ስልጣኑ በትንንሽ ቢሮዎች ውስጥ በትልልቅ ሽኩቻዎች የተጠመደ መሆኑን፣ በመርህ የማይመራና በገዢው ፓርቲ መግለጫ ላይ እድሜ ዘላለሙን መንጠልጠሉን ፣መደማመጥ የተሳነውና ራሱን ለማየት ዝግጁ ያልሆነ፣ ስሜታዊና ግልብ እንዲያው በጥቅሉ መታደስ የሚያሻው አሮጌ መሆኑን በሚገባ መንገድ በራሳቸው ጓድ ተብራርቷል። ሙሉውንም ትርክታ ከላይ ከተገለጸችው መጽሄት ቢ መለከቱ የአዲሱ አመት ተሃደሶ እና ለውጥ አስፈላጊ የሚሆነው የት ሰፈር እንደሆነ በቀላሉ ለመገንዘብ ይችላሉ።

ከፖሊሲም ጋር ተያይዞ ለተነሳው የለውጥ ምኞት መታደስ የሚገባው የኪራይ ሰብሳቢነት አጀንዳ ነው። የመሬት ጉዳይ ብዙ የተባለለትና ኪራይ ሰብሳቢ ሃይሎች በምርጫ ተቀናጅተው ሊቀራመቱት የመጡበትን እና ሳይሳካ የቀረበትንም አጋጣሚ አንዘነጋም። መሬት የህለውናና የፖለቲካ ጉዳይ እንጂ የኢኮኖሚ ብቻ አለመሆኑ ግልጽ መሆን ይገባዋል። የመሬት ይሸጥ ይለወጥ ጥያቄም ከኪራይ ሰብሳቢነት እና ከኢኮኖሚ ፍላጎትም ባሻገር ፖለቲካዊ ስርዓቱን እና ፌዴራላዊ ስርዓቱን የመናድና ህገመንገስቱንም የመገዳደር ጠያቂ ነው። ስለሆነም መታደስና ለውጥ የሚገባው ነጥብ የገዢው ፓርቲ በመቃብሬ ላይ የሚለው ጉዳይ ሳይሆን መሬት ካልተሸጠና ካልተለወጠ የሚለው የ22 ዓመታት ማላዘን ነው። የአዲሱ አመት ምኞቴም ይኸው ነው።

የጸረ ሽብርተኝነት ህግንና የፕሬስ አዋጁን በተመለከተ የተነሳው ደግሞ ከወዲሁ ሊታሰብበት የሚገባው ነጥብ ነው። ምክንያቱም እነዚህ አዋጆች በተራኪውና በመጽሄቱ "የተጠሉ እና የማያዛልቁ ህጎች" የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋልና ነው።

በመጽሄቱ የተጠላ የተባለው የፕሬስ አዋጅ በኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ሃሳብን በነፃ የመግለጽና የመገናኛ ህዙሃንን ነፃነት የተረጋገጠ በመሆኑ፤ መገናኛ ብዙሀን በነፃነት ለመንቀሳቀስ ይችሉ ዘንድ የቅድመ ምርመራ ገደብ እንዳይጣልባቸው ህገ መንገስቱ ዋስትና የሰጠ መሆኑን በአጽንኦት በመገንዘብ፣ የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም፣ ብሄራዊ ደህንነት'፣ የህዝብ ሰላምና ፀጥታን እንዲሁም ሌሎች ተነጻጻሪ መብቶችና ጥቅሞችን ለማስጠበቅ ሲባል በግልጽ በሚደነገጉ ህጎች ብቻ ሃሳብን በነፃ በመግለጽና በመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ላይ ገደቦች እንዲጣሉ የሚያዘውን ህገ መንገስታዊ መርህ በማረጋገጥ ።

በዜጎች መሃከል በሚደረገው ነፃ የሃሳብና የመረጃ ልውውጥ እንዲሁም በመገናኛ ብዙሃን የአሰራር ነፃነት ላይ መሰናክል የነበሩ ተቋማዊ እና መዋቅራዊ ችግሮችን በማስወገድ በነፃ ሃሳብን የመግለጽና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን አስመልክቶ ያዳበራቸውን አዎንታዊ እና ገንቢ ልምዶች የመጠበቅና ይበልጥ የማጠናከርን አስፈላጊነት በመረዳት።

በሃገራችን ዴሞክራሳያዊ ስረዓትን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ስኬታማ የሚሆነው መተኪያ የሌለው ታላቅ ሚና መጫወት የሚችል ራሱን በከፍተኛ ስነ ምግባር በማነፅ በከፍተኛ ሙያዊ ብቃት የሚንቀሳቀስ ነፃና ፈርጀ ብዙ የመገናኛ ብዙሃን ሲኖር ብቻ መሆኑን በመገንዘብ።

በመገናኛ ብዙሃን በህገ መንገስቱ ለተረጋገጡ መሰረታዊ ነፃነቶችና ለወጣቶቸ መብቶች መከበር እንዲሁም ለሰላም፣ ለእኩልነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ የቆሙ መሆኑን ወዘተ በመረዳት እና ግነዛቤ ውስጥ በማስገባት የተደነገገን አዋጅ "የተጠላ" ነው በሚል መዳፈር በርግጥም ተሃድሶ የሚያሻውና ህዳሴውም ከአዲሱ አመት እንዳያልፍ የምንመኘው ነው። የፀረሽብርተኝነቱም አዋጅ በተመሳሳይ ለዜጎች እና ለሃገር ደህንነት ሲባል ያካተታቸውን ሃሳቦች ከግምት በማስገባት ምንጠላው ሳይሆን አስፈላጊያችን ነውና የምትጠሉት ሁሉ እራሳችሁን ታድሱ ዘንድ እንሻለን

በህዝብ ዘንድ እንዲመጣ የተፈለገውና የአረቡን አለም አብዮት እንዲደግም መልክት በማስተላለፍ የተደመደመው ነጥብ "የሞኝ ዘፈን መልሶ መላልሶ ---"እንደሚባለው ቀድሞ ነገር ህዝባዊ መሰረት የሌለውን አብዮት ዛሬማ እነርሱም የአብዮቱን ኪሳራ እየተጋቱ ባሉበት ሰዓትም ላይ ያንኑ ጥሪ ማስተላለፍ መታደስ የሚገባውና ህልመኛ ፖለቲካ ነው። የሃይማኖቱም ነገር ተመሳሳይ ነው። በእስልምና ሃይማኖት ሽፋን የተደረገውን እና እየተደረገ ያለውን ሁሉ ዓለም አውቆታል። አውቆትም ሳያበቃ አውግዞታል። መፍትሄውም እንደአዲስ ጉዳይ መፍትሂ አልባ አስተያየትና ስርዓቱን ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጋር ዝምድና ያለው ለማስመሰል የቀረበው እሳት ሳይሆን በሰሞኑ የሃይማኖቶች ጉባኤና በህዝቡ ሰላማዊ ሰልፍ ከመንግስት ዴሞክራሲያዊነት እና ህገመንግስታዊነት በመነጬ አገባቦች ተገኝታል።

በተለይ ክርስትናን እና እስልምናን ለማጋጨት በአዲስ ጉዳይ በኩል የተሰነዘሩት ተደጋጋሚ ፀብ አጫሪ አስተያየቶች በአዲሱ አመት ሊታደሱና ሊለወጡ ግድ የሚላቸው ይመስለኛል።